# <u>ጥላሁን ገሠሠ --ከትዝታ ማህደርና የከያንያን ሚና</u>

ሀማ ቱማ

የኢትዮጵያ አንጋፋውና ታላቁ ዘፋኝ ጥላሁን ገሠሠ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ ሲባል ከልጅነት ዕድሜያችን ጀምሮ ስናደንቀውና ዘፈኖቹን በህግ መከልከል በሚገባው ድምፃችንም ልናጎራጉር ስንሞክር ዓመታት ያስቆጠርነው የሚሰማን ሀዘን በቀላሉ የሚገመት አይደለም። በጥላሁን ዘፈን አድገናል ብንል ስህተት አይሆንም። አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ሳለን ቅዳሜ ቅዳሜ በክቡር ዘበኛ ሰፈር እነ ጥላሁን፣ ማህሙድ፣ ብዙነሽና ሌሎችም ለወታደሩ በነፃ ዘፈን ሲያቀርቡ ጋሼ ይዘውኝ ይግቡ እያልን ወታደሮችን ለምነን ወይም በአጥር ዘለን ገብተን የጥላሁንና የሌሎቹ ንም ዘፈን እንሰማ ነበር። የሰፈሬ ወጣት የነበረውንና ዛሬ ሕዝብ ቅር የተሰኘበትንም ማህሙድና ሌሎችንም ብናዳምጥም በበኩሌ ከወንድ ዘፋኞች ጥላሁን ከሴት ዘፋኝ ደግሞ ብዙነሽ በቅድሚያ የምወዳቸው ነበሩ። አዲስ ዓመት ዋዜማ ደግሞ በኃይለስላሴ ቲያትር የነጥላሁን አዳዲስ ዘፈኖች ሲቀርቡ ገንዘቡም ለማምሸት ፍቃዱም ባይኖረንም በራዲዮ አማካይነት በጉጉት ስናዳምጥ እንደነ በር ትዝ ይለኛል። በነገታወም በየሻይ ቤቱ ለማዳመጥና ለመዝፈን ለመሞከር ያው ሩጫ ነበር።

በግለሰብ ደረጃ ጥላሁን ገሠሠን ባላውቀወም ባደግኩበት ሰፈር ነዋሪዋን አሥራቴ የተባለች የመጀመሪያ ሚስቱን ግን አስታውሳታላሁ። ጥላሁንም ዓለማየሁ እሸቴም መልከ መልካም ስለነበ ሩ ሴቶች በተለይ ይወዷቸው ነበር። ዓለማየሁ ደግሞ በተማርኩበት በአርበኞች ትምህርት ቤት ተማሪ ስለነበርና የቴክሳስ ሻይ ቤትም የዘመኑ “ ቄንጠኛ” ደምበኛ ስለነበር እሱም በጣም የምና ደንቀው ዘፋኝ ነበር። በዘመኑ በሆሊውድና በአሜሪካ ተፅዕኖ የተነሳ ኤልቪስ አልቪስ ይባል የነበ ረበት ጊዜቢሆንም (ካልተሳሳትኩ የዓለማየሁ ሉጫ ፀጉር ፍሮሙም ከመ ኤልቪስ ነበር) የሀገራች ንን ዘፋኞች እንወድ እንደነበር የሚካድ አይደለም፡ ስለዚህም ጥላሁን ለዚያን ዘመን ልጆችና ወጣቶች ዋናውና ተወዳጅ ዘፋኛችን ነበር። ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ፣ ስናድግና አወቅን ስንል ያኔም ቢሆን ጥላሁን ለብዙዎቻችን ተወዳጅ ሆኖ ቀጥሏል። በዘመነ ደርግ ለረሀብተኛው ወገኑ የዘ ፈነውም ዘፈን ልብን የሚነካ ነበር። በዚህም በዚያም ዘፈኑ ሳንሱሮችም ችግር ይፈጥሩበት እንደ ነበር ይታወሳል። ጥላሁን ከልዩ ድምፁና ችሎታው ባሻገር ሰፊ ተወዳጅነትን ያስገኙለት ዘፈኖቹ በርካታውን ዜጋ--በተለይም ከተሜውን-- የሚኮርኩሩ በመሆናቸው ነው። “ አትመልከቺ ሱፍ አትበዪ መኪና/ እኔም እገዛለሁ ዕድሌ ሲቃና” እየሰፋ የመጣውን የመደብ ልዩነት ያንፀባረቀ የወቅቱ ንዑስ ከበርቴ እሮሮ ነበር። የከተሜውና አልፎም የሰፊው ሕዝብ ኑሮ እየከበደ በመሄድ ላይ ነበርና፣ ሹም ለሹም ይጎራረሳል፣ድሀ ለድሀ ይለቃቀሳል ነበርና እውነታው ቀቢፀ ተስፋን በዘ ፈን አጅበው በሚተርኩ የህንድ ፊልሞች ተመስጠን እንባ እንራጭ እንደነበረው ሁሉ የጥላሁንና የሌሎቹም ዘፋኞች ቃላት የብዙዎቹን የልብ ውስጥ ስሜት አንፀባርቀዋል ማለትም ይቻላል ። እይዋት ስትናፍቀኝ አጠገቤ እያለች ዓይነት ስሜት፣የሀብታም ልጅ ሲጫወት የድሀ ልጅ ይሞታል ምፀት።ጥላሁን አልቻልኩምን ሲዘፍንና የ 1953 ቱ የመንግሥቱና ገርማሜ

ንዋይ መፈንቅለ መንግሥት መጥቶ የብዙ ወጣቶችን ህይወት አቅጣጫ ሲለውጥ፤ እልም አለ ባቡሩ ወጣቱ ይዞ በሙሉ ሲዘፈንወዘተ ከቃላቱ ፖለቲካዊ መልዕክት ፈልቅቆ ማውጣቱ ዋና ስራ ነበር። ዘመኑ የንግግር ነፃነት የተከለከለበትና ሁሉም ትችት ፖለቲካ ተብሎ ፤ክብረ ነክ ተብሎ ሊያስቀጣ የሚችል እንደነበርም ማስታወስ ይገባል። በአጭሩ ጥላሁን ዘፋኛችን ነበር።

ፖለቲካን አወቅን፤ ቅርፅና ይዘትን፤ ላዕላይና ታህታይ መዋቅርን፤ የአብዮት ህግጋትን፤ የለውጥ ውሰጠ ምስጢሩን ወዘተ ተረዳን ብለን ወደ አመፅ ስናዘነብልም የዘፈኑን ይዘትና የዘፋኙን የግል ማንነት ከዘፈኑ መለየት ይቻላል፤ ይገባልን በሚለው ላይ ክርክር መቅለጡ አልቀረም። ጥላሁን በጨለማው ጊዜ በኢሕአፓ ደጋፊነት ቢያዝም የፖለቲካ ሰው ነበር ማለት አይቻልም። ከሶሻሉ ወደ ፖለቲካው ዘንበል ያሉ ዘፈኖቹ አልነበሩትም። የወታደር ልብስ ለብሶ ከነማህሙድ ጋር ጦሩን የሚያደፋፍር ዘፈን ቢዘፍንም በመሰረቱ እማማ አሠፓ አደዬ ወያኔ ሲል አልተደመጠም። በእርግጥ የአንድ ጨቋኝና አረመኔ ስርዓተ ታዛዥ የሆነ ሠራዊት የሀገር ሠራዊት ሊባል ይቻላል ወይ የሚለው ጥያቄው ትላንትም ዛሬም ወቅታዊ ነው። ከግሉ ዕይታና ወዳጅነት በመነሳት ሕዝብ የማይወደውን ቱጃር ቢያሞግስም  በዚህ የተነሳ ለምሳሌ ማህሙድ ወያኔን ደግፎ በይፋ ሲናገር ሕዝብ የተቆጣው ቁጣ አልደረሰበትም። በዘመነ ደርግ ዓለማየሁ እሸቴም ታጣቂ እንደነበር የሰማነውን ስናስታውስ ደግሞ ጥላሁን ብዙ የሚመረርበት አልሆነም።ጥላሁን ዛሬ እንድርያስ እሸቴና ወያኔ የለጠፉበት ዶክተር ተብዬ ቅዕል ሳይሆን የሚገልፀው ሕዝብ ለእሱ ያለው ፍቅርና ቀና አስተያየት ነው ቢባል ትክክል ነው። ጥላሁን ዕድሉ ሆኖ ቢያጠፋም እንኳን ብዙ ሰው ሊያከርበት አልፈቀደም።

በጥላሁን ዘፈን ያደግነውን ወጣቶች አንዳንዶች በደፈናው ሀገሩን የጠላ፤ የባዕድ ባህልና ወግ ያፈቀረ  ወዘተ ብለው ይኮንናሉ። ዘመኑ ተፈታታኝ አልነበረም ብንል ሀቅን መካድ ይሆናል። ትምህርትና ዘመናዊነት ከምዕራቡን ማምለክ ጋር እንዲያያዝ አገዛዙም ሆነ ያኔ የበላይ የነበረው አሜሪካ ሞክረዋል። ያ ጥላሁንና መሰል የሀገር ዘፋኞችን ይወድ የነበረው ትውልድ ግን የዚህ “ አንጎል አጠባ ” አሳዛኝ ሰለባ አልነበረም። ዕቃ ሲወድቅባቸው ኤልቪስዬ ይሉ የነበሩት የገገርው መደብ ሞልቃቂዎች ነበሩ። ብዙዎቻችን ከተሜዎችም ሲኒማ አምፒር ወይ ሲኒማ አድዋ ሄደን አሜሪካው ሆነ ፈረንጁ ዋና ተዋናይ/ አክተር ደቡብ አፍሪካዊውን ሆነ የአሜሪካን ህንዶችን ሲገድል ስናጨበጭብ እንደነበር የምንክደው አይደለም ። ይህን ሊጫንብን የነበረን ፈረንጅ አምላኪነትን ተቋቁመን በፈረንጁም በስርዓቱም ላይ አምፀናልና ዛሬ አሜሪካ ወይ ሞት ለሚሉ ምሁር ተብዬ ግብዝ ተቺዎች የምንጠይቀው ይቅርታ የለም። እኛ በልጅነታችን ነፃ አስተሳሰብ ልንቀማ ቢዘመትብንና በተወሰነ ደረጃ ብንደናገርም አይፈረድብንም --ይልቁንስ ዛሬ ከዚያ ሁሉ ተመክሮ በኋላ ለባዕድ አምልኮ ሰለባ የሚሆኑት ነው ጉድ ሊባሉ የሚገባቸው። የፍሬው ኃይሉ ኢትዮጵያ ሀገሬ፤ የካሳ እንጉርጉሮዎች፤ የአሰፋ አባተ አባይ ዳር ነው ቤቴ፤ የጥላሁን ለእውነት እሞታለሁ አልሳሳም ለነፍሴ፤ የዘመኑ

ኢትዮጵያዊ ደራሲዎች መፅሀፍት፤ የቀኃሥ ቲያትር ቴድሮስ (ከትምህርት ቤት ተወስደን ያየነው) ማንነታችንን እንዳንስት የማይናቅ አስተዋፅዖ አድርገውልናል:: በየካቲት 12 የሰማዕት መታሰቢያ ቀን ፈረንጅ በአዲስ አበባ መንገድ አይወጣም ሲባል የምናስታውስ ነን::

ጥላሁን አረፈ ሲባል ትዝታችን የዚያ ዘመን ነው:: ዶሮ በስሙኒ ቢሸጥም ይጎረብጥ የነበረ ጊዜ:: በየጊዜው አብረውን ያደጉና አብረን የጥላሁንን ዘፈን ልንዘፍን እንሞክር የነበርነው ወንድሞች፤እህቶችና ጓዶች ተለይተውናል:: አልቅሰን ልንቀብራቸው ቀርቶ የት እንደ ተጣሉም ማወቅ አለመቻላችን ዘላቂ ፀፀት ሆኖ ያቃጥለናል:: ትዝታችን ብዙውን ጊዜ እንባ ና ሀዘን አዘል ነው:: ጥላሁን ታሞ ሲሞት ጓዶች ወንድሞች አህቶቻችን ደግሞ በሽብርና በአጋዚያን ተጨፍጭፈዋል፤ በዱር በገደሉ ተሰውተዋል፤ ወላጆቻቸው ገና አርጂ-- ነጋሪ የሚጠብቁም አሉ::ትላንት ጥላሁንን ይሰድቡና ያጥላሉ የነበሩ ወያኔዎች ከነ ቁንጮአቸው ለጥላሁን እረፈት የሀዘን መልዕክት መግለጫ ማሰማታቸውና ማውጣታቸው ቢያንስ ይህ ተወዳጅ ዘፋኝ የሕዝብ ድጋፍ ስላለው ምንኛ በትላንት ውግዘታቸው መቀጠሉ አስቻገሪ እንደሆነባቸው የሚያሳይ ነው:: ጥላሁን ግን በመሰረቱ የኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ዘፋኝ ስለነበር ወያኔዎች ዛሬ ሊያደንቁት ቢነሱ ማንም የሚሞኝ አይኖርም:: ወደ ዘፋኞችና ከያኒያን ሚናም በጥቅሉ ስንገባ በዘመነ ስታሊን ሰፍኖ የነበረው ቅኝት ዓይነት ሁሉም ዘፈን "ታሪክ ሰሪውን ሰፊ ሕዝብ ብቻ ያወድስ" የሚል ቀኖና ባናስተናግድም ዘፋኞች ስለ ሀገራቸውና ሕዝባቸው ሁኔታ በመዝፈን ሕዝብ በተለይም ወጣቱ ትውልድ ንቃት፤ ድርጅትና ትግል አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ መፈለጋችን ተገቢና የሚጠበቅ ነው:: አለ ነገር የሚሉን፤ አዲስ ንጉስ እንጂ መቸ ለውጥ መጣ የሚሉን፤ ተነሱ ተባበሩ ኢትዮጵያን አድኑ የሚሉንን ዘፋኞችን እንፈልጋለን:: ዜሮ ቀፎ ሆነው ለወያኔ አሚና የሚሆኑትን መስሚያ ጆሮ ሊኖረን አይገባም:: ስለ መቻቻል፤ ስለፍቅር፤ ስለ አብሮ መኖር፤ ሰለ መተሳሰብና መደጋገፍ የሚዘፍኑ ያብቡ እንላለን:: ለታሰሩት፤ ለተጋዙት፤ ጨለማ ቤት ለታጎሩት ድምፅ የሚሆኑ:: መጪውን ትውልድ የሚያስተምሩ በቀና ሀገር ወዳድነት የሚያንፁ ዘፈኖች:: ወደድኩሽ ሞትኩልሽ ቁመናህ መልክህ አየባል አይዘፈን ማለት ሳይሆን ከትኩረት አንፃር የባህልና ኪነት መስክም የትግል ዋና መስክ መሆኑን መቸም አለመርሳት ለማለት ነው:: በዘፈናቸው ተወዳጅ ሆነው ሀገርና ወገንን የረሱ ወይም  የግል ጥቅማቸውን ያስቀደሙ ዘፋኞችና አልፎም ለወያኔ ከበሮ መችና ዘፈን ጯኺ የሆኑትን ግን ማቀፍ ሆነ መውደድ ተገቢ አይደለም:: ለዚህም ነው አንዳንድ ዘፋኞች ከወያኔ ጫማ ስር ሲደፉ የደረሰባቸው ማዕቀብ ትክክል የነበረው:: ዛሬም ወጣቱ ቴድሮሰ ካሳሁን ይፈታ ጩኸት የደመቀው ይህ ወጣት በዘፈኑ ሀገርና ሕዝብን ማስታወስ በመቻሉ ነው:: ጥላሁን ለዘፋኞች ምሳሌና አርአያ ነው--በድምፁና በችሎታው:: ከዚህ ባሻገርና በላይ ግን ኢትዮጵያ ስለሰቆቃዋ ስለ ሕዝቧ ብሶትና ምኞት ፍላጎት የሚዘፍኑ፤ ወጣቱን በሀገር ፍቅር የሚቃኙ ዘፋኞችን ትፈልጋለች:: አትነሳም ወይ የሚሉ፤ ታሪክ ይፍረደን የሚሉ፤ ለእናት የሀገር የተሰዋችሁ አይረሳን ውለታችሁ ብለው የሚዘፍኑን ትፈልጋለች::

ሚርያም ማኬባ የዘፈነችው የጥላሁን ዘፈን መጥተሽ ብትጠይቂው ይነግርሻል ምን ጊዜም አይረሳም ያስታውሳል የሚለውን ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥላሁንን አይረሳውም። በቃሊቲ መከራ የሚቀበለውንም ወጣት ዘፋኝ ቴድሮስንም አይረሳም። ስለ ቀይ ሽብርና ያ ጀግና ትውልድ ያንግረጎረውንም ምኒሊክ ያስታውሳል። የወያኔ ዕምቢልታ ነፊዎችና ሆዴ ይቅደም ዘፋኞችንም አይረሳቸውም። ማዕቀቡንም ያጠናክርባቸዋል። በርግጥ ዛሬ ምግብ ጠፍቷል ግን ምግብማ ሞልቷል ያለውና የፍቅርን ማጠጥ የዘፈነው ጥላሁን መልዕክት ወርቁ ከተፋቀርና ከተግባባን ጠላትን በጋራ እናሸንፍና ፍቅርን በክፍፍል ፈንታ እናሰፍናለን በሚል ሊተረጎም የሚችል ነው። ለሚበሰብስ አፈር ለሚሆን ገላ ከመገዛት ሀገርን ማስቀደም። ተስፋ መቁረጥን ወይም " አቅሞን አውቆ መኖር ጥሩ ነው/ ታላቅ ችሎታ ነው" የሚለውን ሽንፈተኛነትን ጥሎ ወንድሜ እህቴ ጓዴ ተባብለን/ኢትዮጵያን ከጥፋት እኛ እናድናለን/ ብሎ ቆርጦ መነሳት።

ጥላሁን ለልጅነታችንና ለህይወታችን ውሱን ደስታ ላደረገው አስተዋፅዖ ሁሌም የምናስታውሰው ይሆናል። ቤተሰቡንና የሚወዱትን ሁሉ ተፅናኑ እንላለን።